## 2ኛ ሺህ   ምእተ አለም የተገጠመ

ዘመንሽን በተስፋ!

ቀናት ቀንን ቆአጥሮ አመት አስከትሎ
ሳይያዝ በልጉም የሸምጡን ጋልቦ
ሁሌም ሲፈራረቅ የእለቱ ወቅት
ደርሰ  ሊነጉድ  የምአቱ አመት፤

ደግ ክፉ ሳይል ሁሉን እንዳመሉ
ተቀብሎ ሲሸኝ ፍጡርን በሙሉ
አንተ ትብስ አነቺ ብሎ ሳይለየን
የድሜ ገደብ ሰጥቶ እኛን ሲያቆየን፣

ለራሱ አሳሳፊ የእድሜ ባላባት
ጠባቂ ተመፅዋች የእግዜር ዳግም ምፃት
ሁሉን ቻይ ገዳቢ ቀንን አሳዋቂ
አሮጌን ካዲሱ ዘመን አስታራቂ፣

የአመታቱ ንጉስ የጊዜው ነጋሲ
የህበሾች ታሪክ የቀኑ ውዳሴ
ይኸውና መጣ ታሪክን አገባ
አላፊውን ወስዶ አዲሱን ሊያጠባ፣

እስኪ ተጠየቂ አንቺ እናት አለም
ምነው ያልተለወጥሽ ታሪክሽ ሲታለም
ከሁሉ ስትቀድሚ ዝናሽ እንዲያ ሲናኝ
እድሜና እድገትሽ ያልሆነው ተመጣኝ
ከቶ ለምን ይሆን የሆንሽው ላባካኝ?

ጥሩ ፍሬ አፈርትሽ የሚሆን ጎምዛዛ
ለምም ስትሆኚ በረሀሽ የበዛ
እድገትሽ የሃሊት ሀብትሽ ምን ቢበዛ
ተፍጥሮሽ ለራስሽ መከራን የገዛ፣

ወልደሽ መካን የሆንሽ ልጅ የቀለደብሽ
ክፉውን ባትፈጥሪው ከመልካሙ ጎንሽ
መች እንዲህ ይሆን ነበር ለእድገት እንቅፋትሽ፣

አንዱን ስትሾሚው ሳትጠቀሚበት
አይምሮ ሳትስጨው አንቺን ሚረዳበት
ስልጣን ብቻ ለምን የሚታበይበት
ካንችው ውስጥ ወጥቶ አንቺን  ሚጎዳበት፣

እድገተ ቆለቆል ህዝብሽ የተጎዳ
ዘላለምሽ ለቅሶ መከራና ፍዳ፣

ደስታሽ ጊዛዊ ማአዛ የራቀሽ
ታሪክና እድሜ የአልተመጠኑብሽ
እዴት ይሆን ይሆን አዲሱ ዘመንሽ ?

ደስታ ነው ለቅሶ ወይስ ልታስመስይ
አንጀትሽ ርሶ በደልሽ ሳይታይ፣

ልክ እደሞላልት ቀደምቱ ታሪክሽ
ሁሌ እንደሚባለው እንዲተረክልሽ!
ነው እንዴ እናት አለም ? ያንቺ ማንነትሽ

ባግባቡ ምሩልኝ ሳትያቸው ቀርቶ
እንዳሻ ሲያደርጉሽ ልባቸው ጎምጅቶ

ከኔ ወድያ ላሳር አምልኮ ሲያደርጉ
በስመ መሪነት ውስጥሽ ሲመሰጉ

ከጓዳሽ እርቃንሽ ወጥቶ እየታየ
መረሽም ሲታበይ አይቶ እንዳላየ
እረ ስንት አለፈ አረ ስንቱ ታየ ?

አንዱ ሊጠግንሽ ከላየ ታች ሲማስን
ሊላው በተንኮሉ ለጥፍት ሲፋጠን
ገዳይ ፍሙን ይዞ በጉያሽ ሲዳፈን፣

አሳት ወላፍኑ አካልሽን ሲበላው
ምነው ከልካይ ያጣሽ ፍሙን የሚያከስመው?

አዳኝና ታዳኝ ባንድላይ ሲውሉ
አሳት ከጨድ ሆነው እስካሁን ሲብላሉ
በውስጥሽ አቁሩሽ ሁሉን የታቀፍሽው
ምን አይነት እናት ነሽ ከሁሉ የደርሽው፣

መቼም ወልዶ አይጥሉ ቢባል ለየቅሉ
ካካልሽ ካልወጣ አጥፊሽ ተግተልትሎ

ምኞት ካሳደረ ዘመንሽን ሊሻገር
ለመኖር ካለመ ከእድሜሽ ጋር ሊቆጠር
ምኑን ምእት ሆነ ነው እንጂ የቁም ፃር፣

ዘመንሽ ዘምኖ እድሜሽ ሳይጣጣም
እስካሁን ስትኖሪ ምእትሽ ቢመጣም
የቀንሽ መቁጠሪያ ሰላምን ካልፃፈ
ልጅሽ እንደጥንቱ ሆኖ ካላረፈ፣

አውደ ጥበብሽን እኩል ካለገሰሸው
ላንዱ ስትጨምሪ ላንዱ ካሳነሰሸው

ከድጡ ወደ ማጥ ይገዳል ነገሩ
ውሉ ይጠፋና በሰላም መኖሩ
ምኞት ብቻ ይሆናል እድሜን መዘከሩ፣

ግና ግና ከተነሳሽ ከታላቅ ውድቀትሽ
አዲሱ ዘመንሽ ከቆመ ለእድገትሽ

ሁሉም ይቈምጣል ሲሰደድ ወዳንቺ
ጎጆውን ሊቀልስ ኑሮውን ሊያበጂ

ገናናነትሽም ባለም ይሰበካል
ያኔ ምእትሽም ሁሉም ያከበሩታል
ኢትዮጵያዊነትም በእጅጉ ይፈለጋል

እስከዚያ ግን እኔ ድርሻዬን ልወጣ
በሌላው ስቈምጥ የራስ እንዳላጣ

አጊጠሽ እንዳይሽ ብርሀንሽ ደምቆ
ወደርሽ ጠረኑ ህዝብሽ ላይ ተጣብቆ
ለዘላለም ይኑር ህዝብሽ ተደስቶ
ባንቺ በእናቱ ብልፅግና ረክቶ፣

እኔም እድል ቀንቶኝ ከገፅሽ ባልገኝ
ባንቺ ውስጥ ባልበኖርም ከሩቅ ሆኜ ብመኝ
በረከትሽ ወጥቶ ለኔ ይደርሰኛል
ባለሁበት ምድር ውስጥሽ ይዳኝኛል፣

አንገቴን ሳልደፋ መኖር ጀምራለሁ
እንጉርጉሮን ሳይሆን ደስታሰን አዜማለሁ
ስወጣም ስገባም ላንቺ እቀኛለሁ፤

እናም ኢትዮጵያዬ ይሄነው ተስፋዬ
በህይወት እስካለሁ ለእኔ መፅናኛዬ፣

ልጆችሽ በህብር ሆነው ሲቦርቁ
ሁላቸው ባንድነት ሆነው ሲናፍቁ
አሮጌው ላዲሱ መሰረት ሲሆነው
አዲሱም የጥንቱን ታሪክ ሲጠብቀው፣

ሁላቸው በፍቅር ተሳስበው ሲኖሩ
አንች ለማሳደግ ከልብ ሲዳክሩ
ጥላቻን አርቅው ዘር ሳይመረምሩ
ሴይጣንን አስወግደው ከእግዝሔር ሲዳመሩ፣

ማየት ነው የምሻው ከሩቅ ከማጀቴ
ውስጥሽ ባልገኝም ሆኜ በስደቴ፣

ቆሜ ባላይሽም ሰላምሽን ናፍቄ
ወጌን ብጠብቅም እራሲን አርቄ
ዘመን ባህልሽን ባለም አሳውቄ
አከብርልሸለሁ ምእቱን አድምቄ
የሁለተኛውን ሽህ ቀንሽን ጠብቄ፣
አዲሱ ዘመንሽን በተስፋ ሰንቄ!!!

**ከዘምሳሌ** .06 -08-07